ሐምሌ 20 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 72ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 72ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተዘጋጅተው በቀረቡ የመድን ሥራ አዋጅ እና የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ አዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ የመድን ስራ አዋጅን እና የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅን በአሁኑ ወቅት ለማሻሻል መንስኤ የሆነው በሀገር ደረጃ እየተካሄደ ካለው መጠነ ሰፊ የለውጥ ማዕቀፍ አንጻር የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች በፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመድን ስራ አዋጅን እና የአነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅን ለማሻሻል ረቂቅ አዋጆች አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረቡት ረቂቅ የማሻሻያ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡
2. ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ማረሚያ ቤት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስትንና ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው የወጡ ህጎችን፣ ሃገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም አለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የእስረኛ አያያዝ ደረጃዎችን ባከበረ ሁኔታ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ማስፈጸም በሚያስችል ሁኔታ ማደራጀት እና ማረሚያ ቤቶች የእስረኞችን ሰብአዊ ክብርና መብት በማክበር እንዲሁም የእስረኞች ግላዊ ሁኔታ በሚጠይቀው የፍርድ አፈጻጸምና እርምት ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግና ከህብረተሰቡ ጋር የሚቀላቀሉበትን ስርአት ለመደንገግ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ጠቅላይ አቃቤ ህግ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
3. በመጨረሻም ም/ቤቱ በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረቡትን የተለያዩ የብድር ስምምነቶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ የተገኙት ብድሮች ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙ እና ጫናቸው ያልበዛ በመሆኑ አዋጆቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

//